ሞጁል 5

የኢክሣይዝ ታክስ ላይ የተዘጋጀ

ታህሳስ 2018

ሀዋሳ

ስልጠናው የሚሸፍነው

- የታክሱ ምንነት
- የኤክሣይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች ባህሪያት
- የኤክሣይዝ ታክስ ለምን ይጣላል
- ፍቃድ ስለማግኘት ምን ምን ያሰፈልጋል
- የኤክሳይዝ ታክስ ሰሌት ዘዴ እንደት ነው
- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር




MANMADE FABRICS




Coca-Cola
pepsi
Sprite



Saturated O


Palinkovac
VODKA
MOSKVA
GIN
VECCHIA








FARMASİ








shutterstock.com • 724166641



የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- ኤክሳይዝ ታክስ ማለት ምን ማለት ነዉ ?
- ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች ባህሪት ምን ዓይነት ነው ?
- ኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰበዉ ከማን ነዉ ?
- ኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላዉ እንዴት ነዉ ?

የኤክሣይዝ ታክስ ምንድነው?

- በኦኢሲዲ ትርጉም - በድርጊት፣ በሙያ፣ በልዩ ጥቅም፣ በማምረት፣ በመሸጥ ወይም በመጠቀም ላይ የሚጣል ታክስ

- የተለመደ ዓለም ዐቀፍ ትርጉም - የተወሰኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችበሚመረቱበት፣ በሚሸጡበት ወይም ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚከፈል ታክስ

የቀጠለ...

- **በኢትዮጵያ** -በኢትዮጵያ **በተመረቱ** ወይም ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ የተመረጡ ዕቃዎች እና **አገልግሎቶች** ላይ የሚጣል ታክስ

- ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ(consumption tax) ፍጆታ

የኤክሣይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች ባህሪያት

1. የቅንጦት ዕቃዎች - LUXURY GOOD

- አስፈላጊ በመሆናቸው ሳይሆን የኢኮኖሚ ደረጃን ለማሳየት ወይም አትኩሮትን ለመሳብ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎች፣

(ያለነዚህ ዕቃዎች መኖር ስለሚቻል፣ቁጠባን አያበረታቱም)

2. ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎች - HARMFUL PRODUCT

- በተጠቃሚው ጤና፣ ማህበራዊ ኑሮ እና ኢኮኖሚ ላይ ችግር የሚያስከትሉ ዕቃዎች/የታጢአት ታክስ/

የቀጠለ...

3. ፍጆታቸው የማይቀንስ ዕቃዎች -NECESSARY GOOD

- ዋጋቸው በመጨመሩ ምክንያት እምብዛም የፍላጐት/የፍጆታ መቀነስ የማይታይባቸው ዕቃዎች(inelastic goods)

የኤክሣይዝ ታክስ ከፋዮች በቅ/ጽ/ቤት

- **የተመዘጋቢ ብዛት በቅ/ጽ/ቤቱ 26 ድርጅቶች ብቻ ናቸው**

- በሀዋሳ ኢንዱስትሪል ፓርክ ተመዘጋቢ 17 ድርጅቶች
- በወሃ በማምረት ላይ የተሰማራ 4 ድርጅቶች
- ሱገር ፋብርካ ላይ የተሰማራ 2 ድርጅቶች
- አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ (ሰበታ)
- ቡራዮ ላይ 1 የፕላስትክ ፋብርካ
- ዘብዳር ቢራ በጉራጌ ዞን ላይ

ኤክሣይዝ ታክስ የሚጣልባቸዉ ምክንያቶች

ገቢ ለመሰብሰብ

- የኤክሣይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ፍጆታ ምክንያት የሚደርሰውን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የጤና ችግር ለመቋቋም (በሲጋራ/ የሳንባ፣ በመጠጥ/የትራፊክ አደጋ ወ.ዘ.ተ) መንግሥት የሚያወጣውን ወጪ ለመሸፈን፣

የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ -

- ሰዎች በዋጋው መብዛት ምክንያት እንደ ሲጋራ እና አልኮል የመሳሰሉ ምርቶችን መጠቀማቸውን እንዲቀንሱ፣

የቀጠለ...

- **ሀብትን ለማደለደል** - ሀብታሞች ከሚጠቀሙባቸው የቅንጦት ዕቃዎች ታክስ በመሰብሰብ ድሃው ጎብረተሰብ የሚጠቀምባቸውን የልማት ሥራዎች ለመሥራት

- **አካባቢ ጥበቃ** - በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ እንደ ነዳጅ፣ የፕላስቲክ ዕቃዎች ያሉ ዕቃዎችን አጠቃቀም መቀነስ

ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለበት ሰነ-ሰርአት

- ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፣
- የታክስ ባልስልጣኑ የሚጠይቃቸውን ሰነዶች፣
- የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ፣ ኮንቴይነሮች፣ መሣሪያዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣
- ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የእያንዳንዱን የማምረቻ ሕንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም ሕንፃው፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙበትንሁኔታ እና አካባቢውን፣
- የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፣
- የማምረቻ መሣሪያዎችን ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፣

የቀጠለ----------

- ንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣መተዳደሪያ ደንብ፣ ከምግብና መዲታንት ቁጥጥር የተሰጠዉ ሰርትፍኬት(የሚመለከታቸዉ)
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚችለው ፈቃድ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው
- የታክሱ ባለስልጣን ካልፈቀደለት በስተቀር የተፈቀደለት አከናዋኝ ከጸደቀው ፕላን ውጪ ለመስራት አይችልም።

ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በስተቀር የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አይችልም፡-

- የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሸጊያ ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት፣
- ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትምባሆን ወደአገር ማስገባት፣
- ኤታኖል ወደአገር ማስገባት፣

የኤክሳይዝ ፈቃድን ወይም ምዝገባን ስለማገድ እና ስለመሠረዝ

- ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ፤
- የተፈቀደለት ሰው በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆኑ ተግባራት ላይ ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣
- የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መሣሪያ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ፣
- ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የተከለከለ እንደሆነ፣

የኤክሣይዝ ታክስ ቁጥጥር አጠቃላይ ሁኔታ

- የታክሱ ባለስልጣን ወደአከፋፋዮች፤ ጅምላ ሻጮች እና ቸርቻሪዎች መጋዘን ውስጥ የሚገባ ማናቸውም ማሸጊያ እና መጠቅለያ ባለስልጣኑ በሚያዘው መሰረት የመለያ ምልክት እንደረግባቸው ሊያዝ ይችላል።
- ከኤክሳይዝ ታክስ ሃላፊ ካልተፈቀደ በስተቀር በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በተፈቀደለት መጋዘን ውስጥ ሊቀመጥ አይችልም።
- የተመረቱ ዕቃዎች ከፋብሪካው እስከሚወጡ፣ ከኢትዮጵያ ውጪ እስከሚላኩ፣ ከአገልግሎት ውጪ እስከሚሆኑ ድረስ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፣

- ስልጣን የተሰጠዉ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ዕቃዎቹን በማናቸዉም ጊዜ መመርመር ይችላል፣
  - አምራቹ በፋብሪካው ውስጥ፡-
    - ✓ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ እንዲኖር ማድረግ፣
    - ✓ ለቁጥጥር በሚያመች መንገድ ዕቃዎቹን መመዝገብ፣ መያዝ አለበት፣
-

የመከታተያ ሥርአት-

- የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌላም አስፈላጊ ቦታ ላይ በአማርኛና በአካባቢው የሥራ ቋንቋ፡-
- ✓ “የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ” እና
- ✓ የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት።
- ለይቶ መቆለፍ ወይም ማሸግ፣
- የተፈቀለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት።

የቀጠለ--------

- ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም፣ አለበት።
- የፋብሪካውን እንቅስቃሴ በሩቅ መቆጣጠር የሚያስችል መሣሪያ መግጠም፣
- የአመራረት ሂደትን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣የአልኮል መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎችን ግዴታ ሊጣልባቸው የሚችለው የፋብሪካው የማምረት አቅም በሰዓት ከ500 (አምስት መቶ) ጠርሙስ በላይ ሲሆን ነው።
- በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ የጽሕፈት ሥራ የሚከናወንበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬዕቃ መጋዘን፣ የምርት መጋዘን የተለያየ መሆን አለባቸው፡

የቀጠለ--------

- የታክሱ ባልስልጣን ለመንግስት ገቢ ትክክለኛ አሰባሰብ ሲባል አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አግባብነት ያለው ሰራተኛ የተፈቀደለትን አከናዋኝ የስራ ቦታ በሙሉ ወይም የተወሰነውን የስራ ቦታውን ክፍል እንዲቆልፍ፤ እንዲያሸግ ወይም ሌላ ማናቸውንም የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ እና/ወይም የፈሳሽ መለኪያን፤ ካሜራን፤ አውቶማቲክ ባር ኮድ ፤ስካነር እና በኮምፒውተር የታገዘ ስካን እና የመሳሰሉትን እንዲጠቀም ሊያደርግ ይችላል።
- የተፈቀደለት ሰው በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት መግጠም አለበት።

በምርቶች፣በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት ስለማድረግ

- ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማሸጊያዎች ለመከታተል እና ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል።፡

- ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚይዝ እያንዳንዱ ማሸጊያ ወይም መያዣ ወይም መጠቅለያ በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል፡-

ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን አገር የሚያሳይ ፅሑፍ፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣“ለአገር ውስጥ ፍጆታ” የሚውል የሚል ፅሑፍ፣

ሐ) ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ “ከታክስ ነፃ” የሚል ፅሑፍ፣

በጥሬዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

- ለማምረት የሚውሉ ጥሬዕቃዎች መጠናቸውን በትክክል ለማወቅ ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን ማስቀመጥ፣
- ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይችልም።
- የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቲል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው መሠረት ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይችልም

ከሂሳብ መዝገብ አያያዝ ጋር ለኤክሳይዝ ታክስ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- የተፈቀደለት አምራች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** ድንጋጌዎች መሠረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት
- ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር
- በወሩ የተመረቱ፤ የወጡ፤ በምርት ሂደት ላይ ያሉ እንዲሁም ወደምርት ያልገቡ ጥሬ ዕቃዎች ዝርዝር
- የግብዓት ምርት ጥምርታ ለእንዳንዱ የምርት አይነት
- የብክነት መጠን መግለጫ
- ውዳቂ ምርቶችን፤
- የየእለቱ የኤክሳይዝ ታክስ ማጠቃለያ ሰነድ

ሠ. ተመርተው ወደ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች፤

ረ. የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ እቃዎች፤

ሰ. የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ እቃዎች፤

ሸ. በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎች

- ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎች የተሟላ መረጃ
- የጠፉ እቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ ማቅረብ
- ቆጠራ ከመካሄዱ **14** ቀናት በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ማሳወቅ

- የተመላሽ እቃዎች መመዝገቢያ እና ማስታረቂያ
- በሽያጭ ከፋብሪካ የወጡ እቃዎች ዝርዝር በዓይነት በብዛት በወጪ በትርፍ ህዳግ እንዲሁም በዋጋ
- ሽያጭ ሳይኖር ከፋብሪካ የወጡ እቃዎች ዝርዝር በዓይነት በብዛት በወጪ በትርፍ ህዳግ እንዲሁም በዋጋ
- ከታክሱ ነፃ ለሆኑ የተሸጡ እቃዎች ዝርዝር
- ተመላሽ የሆኑ እቃዎች ከነተሸጡበት ደረሰኝ እንዲሁም ከተከፈለባቸው ኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር .....

- የሂሳብ መዝገቡን በታክስ አስተዳደሩ ለተመለከተው ጊዜ ጠብቆ ማቆየት አለበት።
- በገቢ ግብር አዋጁ፤ በታክስ አስተዳደሩ እንዲሁም ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት (176/2014ን ጨምሮ) ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ግብር ከፋይ ፍቃድ ከማገድ ጀምሮ እስከ መሰረዝ የሚደርስ ሙሳኔ ያስከትላል።

ማነቃቂያ ጥያቄ

- What do you know about `fair market value` valuation ?
- **ትክክለኛ የገበያ ዋጋ?**

ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

- ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነዉ የሚባለዉ በዚያን ጊዜና ቦታ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተካሄደ የጅምላ ግብይት ዕቃዉ ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቅ ዋጋ ነዉ፣
- የዕቃው ዋጋ፣ ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ሌላ የተፈቀደለት አምራች ለተመሳሳይ ዕቃዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ሊሆን ይችላል።
- በአንድ በተወሰነ ጊዜ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማወቅ ካልተቻለ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ይወሰናል።

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት ስለሚሆን ዋጋ

- ለታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ወር ከ30ኛው ቀን በፊት በሚቀጥለው ወር ከፋብሪካው የሚወጡ ዕቃዎች የሚቀርበው ዋጋ ዝርዝር ይሆናል።
- ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ለእያንዳንዱ ምርት ዓይነት፣ መያዣ እና የመያዣ ዓይነት የሚኖረውን ዋጋ የሚያመለክት መሆን አለበት።
- ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው ምርቱን ወደገዥው ለማድረስ የ[illegible]ጣውን የትራንስፖርት ሂሳብ የሚጨምር አይሆንም፣

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት ስለሚሆን ዋጋ

- በዋጋ ዝርዝሩ የተገለፀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች ከሆነ ባለሥልጣኑ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ ይወሰናል።
- ዕቃው በዝርዝሩ ከተመለከተው ዋጋ በላይ ከተሸጠ የተሸጠበት ዋጋ፣ መሠረት ታክሱ ይሰላል
- ምርቱ ከመያዣው ጋር አብሮ የሚሸጥ ከሆነ ታክሱ የሚሰላው በጠቅላላው ዋጋ ላይ ይሆናል።

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት

1. ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ ዕቃዎች ፤

- ✓ በዕቃው ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚሠላው የዕቃው ዋጋ(cif)እና
- ✓ በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ(custom duty) ድምር ላይ ነዉ።

...የቀጠለ

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚመረቱ ምርቶች

- ማስከፈያ ዋጋ (የታክስ መሠረት) የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን፣-
  - ✓ በዕቃ አቅርቦት ላይ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
  - ✓ የኤክሳይዝ ቴምብር ወጪ(ካለ) እና
  - ✓ ተመላሽ የዕቃ መያዣዎች ወጪን አይጨምርም፡

የታክስ ስሌት ምጣኔ ዘዴ

1. በቁርጥ (በብዛት ወይም በክብደት) ላይ የተመሰረተ ፡ ፕላስቲክ(103 ብር በኪግ)
2. በዋጋ ላይ የተመሰረተ ፡ ዘይት፤መኪና፤ውሀ
3. በቁርጥ እና በዋጋ ላይ፡ ሲጋራ (30%+20ብር በእሽግ(20 ፍሬ)
4. ከቁርጥ እና ከዋጋ ከፍተኛ የሆነውን፡ ቢራ (40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ የበለጠውን)

...የቀጠለ

ቢራ

በግብአት አይነት -

- **ከብቅል የተዘጋጀ ቢራ- የተስተካከለው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ 40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን**
- **➡ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ተመርቶ በበቀለ ገብስ የተመረተ ቢራ - የተስተካከለው 35% ወይም 23 ብር በሊት ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን**
  - **➡ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በአገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ ቢራ የተስተካከለው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ 30% ወይም 21 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን**

➡በድብልቅ የተዘጋጁ፣ የአልኮል ይዞታቸው ከ7% ያልበለጠ ጥንካሬ ያላቸው መጠጦች - የተስተካከለው 40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን

...የቀጠለ

- **የወይን ጠጅ፣**

በግብአት አይነት ፣

- ዉሃን ሳይጨምር ብያንስ ከክብደቱ 75% የምያህለዉ በአገር ዉስጥ ግባአት የተመረተ የወይን ጠጅ 30 % ነው
- ዉሃን ሳይጨምር ብያንስ ከክብደቱ 75% በታች የምያህለዉ በአገር ዉስጥ ግባአት የተመረተ የወይን ጠጅ 40 % ነው

- **የሚፈሉ መጠጦች ፡**(ሲዳር፣ ፔሪ፣ ኦፓክ ቢራ፤ የሩዝ አልኮል መጠጥ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፤ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ 40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን

- **የሚፈሉ መጠጦች ፡**(ሲዳር፣ ፔሪ፣ ኦፓክ ቢራ፤ የሩዝ አልኮል መጠጥ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፤ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% የበለጠ 80%

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው እቃዎች መጠን

ይህ አንቀፅ ተፈፃሚነቱ ታክሱ የተጣለው የዕቃዎቹን ብዛት ወይም ክብደት መሰረት ባደረገ መጠን በሚሆንበት ጊዜ ነው።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ታክስ ማስከፈያ መጠኑ የሚወሰነው

የእቃውን ማሸጊያ እና በውስጡ የያዘውን ክብደት መሰረት በማድረግ ይሆናል

የቀጠለ...

1. ከእቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ሲሆን እና ማሸጊያው

ሀ. የተጣራ ክብደቱ ያልተፃፈበት ከሆነ ወይም

ለ. በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ካለሆነ

3. የእቃው ባለቤት የማሸጊያውን ትክክለኛ ክብደት ማስረዳት ካልቻለ

የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈለው በማሸጊያው እና በውስጡ በያዘው እቃ ጠቅላላ ክብደት ላይ ይሆናል።

ማስተካከያ ስለማድረግ

- ሚኒስትሩ በአዋጁ በተመለከተው የታክስ ማስከፈያ ምጣኔ ላይ ከ10% ያልበለጠ ምጣኔ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።
- በቁርጥ በተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የዋጋ ንረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት።

ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ

- የታክስ ስሌቱ ግልፅ እና አምራቾች እኩል ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አምራቹ
- የምርቱን ዓይነት፣ የመያዣውን መጠን እና ዓይነት ፣ ለገበያ የሚውልበትን ቦታ (ለአገር ውስጥ ፍጆታ፣ ለኤክስፖርት፣ከቀረጥ ነፃ)በየወሩ ማቅረብ አለበት።
- የማምረቻ ወጪ፣ የትርፍ ህዳግ መያዝ አለበት።
- የዋጋው ዝርዝር አምራቹ ራሱ የሚጠቀምባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ይጨምራል። ይህም ማለት የተጠቀመውን የትምባሆ ቅጠል በኪሎ ግራም ዋጋ በዝርዝሩ መካተት ይኖርበታል

የቀጠለ...

- ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎችሊይዝ ይገባል፡-
- ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበትን ቀን፣
- የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣
- የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ ይህንኑ፣
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፣
- ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣
- የዕቃዎቹን ብዛት፣
- የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ዋጋ፣
- ሊከፈል የሚ[illegible] የኤክሳይዝ ታክስ፣

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ

ሀ/ የተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያመርታቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተመረቱት ዕቃዎች ፡-

- ከአምራቹ ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል።
- በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ጥቅም ላይ በዋሉበት ጊዜ ከፋብሪካው እንደወጡ ይቆጠራል።

የቀጠለ--------

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ አገር የሚያስገባ አስመጪ በሚከተለው ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት፡-

- ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር የነዳጅ ምርቶች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ፣

- ሌሎች ዕቃዎች ፣ ዕቃው ወደ አገር ሲገባ፣

ሐ) ለኤክስፖርት የሚመረቱ ምርቶች ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ሲወጡ፣

የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ እና መክፈያ ጊዜ

- የእያንዳንዱን ወር የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ያለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት
- ማስታወቂያው የእያንዳንዱን ምርት ዓይነት፣ ለሽያጭ ወጥቶ ሳይሸጥ የተመለሰውን፣
- ደረሰኝ፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና የየዕለቱን መረጃ በሚገባ መያዝ፣

የቀጠለ------

- የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን በሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት ፣
- በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎች፣
- የጠፉ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ ከፀጥታ ክፍል ማቅረብ፣
- ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ

ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ እቃዎች

- ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ
- በታክስ ባለስልጣኑ ፍቃድ ከጥቅም ውጪ እንዲሆኑ የተደረጉ ዕቃዎች
- ከኤክሣይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ ዕቃዎች
- ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማህበራዊና ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች በሚኒስቴሩ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች
- ለህክምና አገ/ት እንዲውል ለሰው በመጠጥነት አገ/ት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል

የቀጠለ----

- በሚከተለው ሁኔታ በአደጋ የጠፉ ወይም የተበላሹ ዕቃዎች

  - በመጫን እና ማውረድ ጨምሮ እቃዎቹ ከፋብሪካ በመውጣት ላይ ባሉበት ጊዜ
  - በአምራች ፋብሪካ ውስጥ ባሉበት ጊዜ
  - እቃዎቹ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላን/ በመርከብ በመጋጋዝ ላይ ባሉበት ጊዜ።

በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ማቀናነስ

ከአልኮል፣ ትንባሆ እና ስኳር በስተቀር በሌሎች ግብዓቶች ላይ የተከፈለ ኤክሳይዝ ታክስ በመጨረሻ ምርቱ ከሚከፈለው ኤክሳይዝ ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፣

- የሚቀናነሰዉ ለተሸጠዉ ምርት የዋለዉን የግብአት መጠን የተከፈለዉን ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ብቻ ነዉ

- የኤክሳይዝ ታክስ በደረሰኝ ላይ ተለይቶ የሚታይ ስለሆነ ማቀናነሱ ችግር አይኖረውም፣

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች

- አምራቹ ራሱ ለሚያመርተው ምርት የሚውል የጥሬ ዕቃ ምርት ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይሆናል፣
- ዋጋው ምርቱን ለማምረት የሚወጣው ወጪ እና ለሦስተኛ ወገን ቢሸጥ የሚታከለው የትርፍ ህዳግ፣
- ጥሬ ዕቃው በከፊል ለሌላ አምራች ጭምር የሚሸጥ ከሆነ የተሸጠበት ዋጋ ትክክለኛው የገበያ ዋጋ፣

የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ስለመጠቀም

- አነስተኛው የማስከፈያ ዋጋ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን የአገር ውስጥ ምርቶች ለማምረት የሚውሉት ጥሬ ዕቃዎች በአገር ውስጥ እርሻ የተመረቱ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ መቅረብ አለበት፣
- የሚቀርበው መረጃ፣ የማስረከቢያ ሰነድ፣ ደረሰኝ፣ ከአምራቹ ጋር የተደረገ ውል፣ የአምራቹን ስም፣ አድራሻ ይጨምራል፡
- የተፈቀደለት አምራች ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች ማቅረብ ካልቻለ ከውጭ አገር በሚመጣ ግብዓት ለሚመረቱ የተወሰነው የማስከፈያ ምጣኔ ተግባራዊ ይደረግበታል።

የኤክሣይዝ ቴምብር

- የኤክሣይዝ ቴምብር ማለት በአካለዊ፤ በዲጅታል ወይም በሌላ በተመለከተው መሰረት የኤክሣይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ቴምብር ነው።

የኤክሣይዝ ቴምብር የሚለጠፍባቸው ዕቃዎች

1. የአልኮል መጠጦች፤

2. አልኮልና አልኮል አልባ ቢራ፤

3. የወይን ጠጅ ወይም የተጣራ አልኮል የታከለበት ወይን ጠጅ እና ተመሳሳይ የአልኮል መጠናቸው ከ0.5% በላይ የሆነ ምርቶች፤

4 ለሰው መጠጥነት የሚውሉ እና ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረቱ መጠጦች የአልኮል መጠናቸው ከ0.25 ያላነሰ የአልኮል መጠጦች፤

5. የታሸገ ወሃ

6. ሽቶዎች፤

7. ሲጋራ፤ ትምባሆ፤ ሻሻ

ተመላሽ

- በጉዞ ላይ ወይም በኤክሣይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ሳሉ፤

- ከጥቅም ውጪ የሆኑ፣
- የተሰረቁ፣
- በሽያጭ ውሉ መሠረት ለሻጩ የተመለሱ ዕቃዎች፣
- በዱቤ ከተሸጠ በኋላ ባልተሰበሰበ ዕቃ ላይ የተከፈለ የኤክሣይዝ ታክስ፣
- ፈቃድ በተሰጠዉ ወይም በተመዘገበ አምራች ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት የዋሉ፣
- ኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸዉ በጉምሩክ ስነስርአት ገብተዉ ተመልሰዉ የሚወጡ ዕቃዎች

- ሻጩ ከገዥው ላይ የኤክሣይዝ ታክሱን የተቀበለ እንደሆነ የተመለሰለትን ታክስ ይከፍላል፣

የቀጠለ------

- ተመላሹ ከተከፈለ በኋላ ዕቃዎቹ የተሸጡ እንደሆነ ታክሱ ይከፈላል፣
- ከኤክሣይክ ታክስ ነፃ የተደረገ ዕቃ የተሸጠ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ የዋለ እንደሆነ ታክሱ ይከፈላል፣
- ከታክሱ ነፃ ሆኖ ወደአገር የገባ ተሸከርካሪ ባለቤት የሞተ እንደሆነ ወራሾቹ ታክሱን አይጠየቁም

የእቃ ቆጠራ እና የጠፉ እቃዎች

- በአመት አንድ ጊዜ የተማላ የእቃ ቆጠራ መደረግ አለበት
- በተጨማሪም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሃዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት

ሀ. በየወሩ መጨረሻ በፋብሪካ ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ እቃ እና የመጨረሻ ምርት፤

ለ. አዲሰ ወደ ፋብሪካ የገቡ ጥሬ እቃዎች፤

ሐ. በፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ እቃዎች፡

መ. የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶች፤

የወንጀል ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ፣
- የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ ዕቃዎችን ቴምብር ሳይለጠፍባቸው የተገበያየ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ፣
- በፈቃዱ ከተመለከተው ቦታ ውጪ ሲያመርት የተገኘሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ፣
- ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ዕቃ ወጪ አድርጐ የተገኘ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ፣

የወንጀል ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የሚያመርት፣ የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጥፍ የተገኘ፣ ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ የሚያመርት ከ3-5 ዓመት
- በፈቃዱ ከተመለከተው ውጪ ያለ ዕቃ ሲያመርት የተገኘ፣ ለቁጥጥር አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ያላሟላ፣ ያለፈቃድ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ ይዞ የተገኘ መልሶ የተቀበለውን የኤክሳይዝ ታክስ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያላደረገ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበትን ዕቃ የተጠቀመ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረገን ዕቃ ለሽያጭ ያዋለ ከ3 – 5 ዓመት እና ብር 100,000፣

- በፈቃዱ ከተመለከተው ቦታ ውጪ ያመረተ ከ5 - 7

ዓመት እና ከብር 100,000 - 200,000፣

- የኤክሣይዝ ፈቃዱን ያልለጠፈ፣ ለውጥ ሲኖር ያላሳወቀ ከ1-3 ዓመት

ምሳሌ

1. ብሄራዊ ትንባሆ ድርጅት በብር 1,000,000 ቀረጥ ጨምሮ የትምባሆ ቅጠል ከውጪ ሀገር አስመጥቶ በመጠቀም በወሩ 20,000 እሽግ ሲጋራ አምርቶ ከፋብሪካ ቢያወጣ ፤ እንዲሁም የአንድ እሽግ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ብር100 ብር ቢሆን?

1. ወደ ሀገር ሲያስገባ የከፈለውን የትምባሆ ኤክሳይዝ ታክስ ስንት ነው?

2. ሲጋራ በማምረት ከሚሸጠው የሚከፈለው ኤክሳይዝ መጠን በወሩ ስንት ነው?

3. በወሩ መጨርሻ ለገቢዎች ጠቅላላ በማሳወቅ የሚከፍለው ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ስንት ነው?

መልስ

- የትምባሆ ቅጠል 30% እና ሲጋራ 30% +20 ብር በእሽግ(20 ፍሬ)
- 1. የትምባሆ 1,000,000*30 %=**300,000 በግብዓት ላይ የሚከፈል**
- 2. የሲጋራ (20,000*100)*30%+(20*20,000)=
- 600,000+400,000=**1,000,000 በምርት ላይ የሚከፈል**
- **3. አጠቃላይ በወሩ የከፈለው ኤክሳይዝ ታክስ 1,300,000**

2. ሀ ሁ ሂ.የተ.የግል ድርጅት በብር 1,000,000 ቀረጥ ጨምሮ 10,000 ሊትር ንፁህ አልኮል ከውጪ ሀገር አስመጥቶ በመጠቀም በወሩ ውስጥ 14,000 ሊትር ጂን (40% የአልኮል ጥንካሬ ያለው) ቢያመርት እና ከተመረተው ውስጥ 10,000 ሊትሩን በወሩ ውስጥ ቢሸጥ እንዲሁም የአንድ ሊትር ጂን የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ብር 200 ሲሆን መክፈል ያለበት ኤክሳይዝ ታክስ ?

1. ወደ ሀገር ሲያስገባ በንፁህ አልኮል ግብአት ላይ የተከፈለ ታክስ መጠን ስንት ነው?

2. በምርት ላይ የሚከፈለ ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ስንት ነው?

3. በወሩ መጨርሻ ለገቢዎች የሚከፍለው ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ስንት ነው?

4. የግብዓት ምርት ጥምርታው ስንት ለስንት ይሆናል?

ማስታወሻ

የንፁህ አልኮል 60% እና ጂን 80% (የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ)

መልስ

- የንፁህ አልኮል 60% እና ጂን 80% (የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ)

1. 1,000,000*60 %=**600,000 በግብዓት ላይ የተከፈለ**

2. (10,000*200)*80% =1,600,000 በምርት ላይ የሚከፈል

3. 600,000*71% =428,571 ኤክሳይዝ ታክስ

1,600,000+428,571= 2,028,571 በወሩ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ ነው።

4. የግብዓት ምርት ጥምርታውም?

- አንድ ሊትር ንፁህ አልኮል በመጠቀም 1.4 ሊትር ጂን ያመርታል ማለት ነው።

14,000/10,000=1.4

3. አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ድርጅት በብር 8,000,000 ቀረጥ ጨምሮ 56,000 ሜትር ብትን ጨርቅ ከውጪ ሀገር በማስመጣት በወሩ ውስጥ 40,000 ሸሚዝ ቢያመርት የአንድ ሸሚዝ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ብር 500 ቢሆን ከተመረተው ውስጥ 20,000 ከፋብሪካ ቢወጣ መክፈል ያለበት ኤክሳይዝ ታክስ ?

ማስታወሻ ብትን ጨርቅ 5% እና ሸሚዝ (የተሰፉ ልብሶች) 5% (የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ አለቸው)

1. ወደ ሀገር ሲያስገባ በብትን ጨርቅ ላይ የተከፈለ የግብአት ታክስ መጠን ስንት ነው?
2. በምርት ወይም በተሰፉ ልብሶች ላይ የሚከፈለ ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ስንት ነው?
3. በወሩ መጨርሻ ለገቢዎች የሚከፍለው ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ስንት ነው?
4. የግብዓት ምርት ጥምርታው ስንት ለስንት ይሆናል?

መልስ

1. 8,000,000*5%=**400,000** ሲገባ የሚከፈል
2. (20,000*500)*5%=**500,000** ከምርት መከፈል ያለበት

- 400,000*50%=200,000 ለወሩ የሚቀናነስ በግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ ነው
- **3. 500,000-200,000=300,000** በወሩ የሚከፈል ታክስ ነው፡፡
- **4.** የግብዓት ምርት ጥምርታው**(1.4=1** ማለትም አንድ ሸሚዝ ለማምረት 1.4 ማትር ብትን ወርቅ ይወቀማል)

አመሰግናለሁ